# ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት

International Ethiopian Women's Organization

**www.ewointernational.org**

**IEWO *P.O. Box 56729 Washington DC, 20040***

**Tel. 240 691-4370**

---

*"ሀገርን ለማዳን፡ ህልዉናዋን ለመጠበቅና አልፎም ሁለገብ እድገትዋን ለማረጋገጥ ሴቶች በህብረተሰቡ ውስጥ የሚኖራቸዉ የእኩልነት መብትና የሚያድርጉት የነጻ ተሳትፎ ወሳኝ ነዉ:: "* **ዓኢሴድ**

## የኢትዮጵያዉያን
## ሴቶች ቀን ለኢትዮጰያን በሙሉ ታላቅ በዓል

**ቅዳሜ የካቲት** 29/2000 / March 8, 2008 /
**ከቀኑ** 2 **ሰአት** (2 pm) **ጀምሮ**

በዚህ በሴቶች ቀን በዓል ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት በፖለቲካና በህብረተሰቡ ዉስጥ ጉልህ ሚና የሚጫወቱና ከልዩ ልዩ ቦታዎች የሚመጡ ታዋቂ እንግዶችን ፣ ወጣቶችን፣ በመጋበዝ የውይይት መድረክ አዘጋጅቷል::

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት የተቋቋመዉ ሴቶች መብታቸዉን ለማስከበር መደራጀት እንደሚያስፈልጋቸዉ በተገነዘቡ በመላዉ ዓለም በሚገኙ ኢትዮጵያውያት ሴቶች ነዉ:: የአገራችን ሴቶች ለፍትህ ፣ ለእኩልነት ፣ለእድገትና ለጤንነት ብሎም በሃገራቸዉ ጉዳይ ላይ በሙሉ ዜግነት ለመሳተፍ የሚያደርጉት ትግል ከሌሎች ለዲሞክራሲ ከሚታገሉ ንቅናቄዎችና ድርጅቶች ጋር በመተባበርም መሆኑን በማመን ነዉ:: ሴቶች በሁሉም መስክ መብታቸዉ እንዲከበርና እንዲረጋገጥ የህብረተሰቡ በሞላ ትብብር ያስፈልጋቸዋል::

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን የኢትዮጵያ ሴቶችም ቀን በመሆኑ የአገራችን ሴቶችም አብረዉ በዓሉን በያሉበት አገር ሁሉ ያከብራሉ:: በመሆኑም በዚህ በዋሽንግተንና በአካባቢዉ የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን የመገኘትና በበዓሉ የመሳተፍ ግዴታ አለብን:: የሴቶችም ጥያቄ የሀገር ጥያቄ ነዉና ወገኖች ፥ እናቶች ፥ ወንዶች ሳይቀሩ በዚህ ዝግጅት በመገኘት የበአሉ ተካፋይ ትሆኑ ዘንድ በትህትና እንጠይቃለን::

## የዝግጅቱ ቦታ
## Unification Church
## 16 th Str & Columbia rd. NW
## Washington DC